[illegible] ዲያስፖራ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
[illegible] መዝገብ ቤት
የደረሰበት ቀን 21 ታህሳስ 2007
የመዝገብ ቁጥር
የዶሴው ቁጥር T-30-1

ቁጥር 2.0/75/07
Ref. No.
ቀን 10 ታህሳስ 2007
Date

ለውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ማግኘት የሚችሉበት ሥርዓት ትግበራን ይመለከታል

ባለሥልጣኑ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አሰጣጥ ሥርዓቱን በጣት አሻራ በማስደገፍ የግብር ከፋዩን ማንነት በብቸኝነት ለመለየት የሚያስችል የግብር ከፋይ መለያ ቁጥርና ካርድ በማሰራጨት ላይ ይገኛል፡፡ ሆኖም ይህ አሰራር በውጪ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እንዲሁም የስራና መኖሪያ ፍቃድ ኖራቸው በሀገር ውስጥ በተለያየ የንግድ ስራ ዘርፍ የተሰማሩ ግብር ከፋዮች በፈለጉት ጊዜና ፍጥነት አገልግሎት ማግኘት አላስቻላቸውም፡፡

በመሆኑም ይህን ችግር ለመፍታት ቀደም ሲል በተወሰኑ ቦታዎችም ቢሆን በተንቀሳቃሽ የአሻራ መቀበያ መሣሪያዎች ከሚሰጠው አገልግሎት በተጨማሪ የተመዝጋቢዎችን መረጃና አሻራ ካሉበት ቦታ በወረቀት በመቀበል ወደ ሥርዓቱ እንዲገባና ተጠቃሚዎች አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችል አሰራር ለማስጀመር የተለያዩ ተግባራት በጋራ ሲከናወኑ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡ በዚሁ መሰረት በባለሥልጣኑ በኩል መከናወን የሚገባቸው ተግባራት የተጠናቀቁ በመሆኑ ሥርዓቱን ለማስጀመር እንዲቻል የአሰራር መመሪያውንና (Guideline) ተጨማሪ መረጃዎችን ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን ሲሆን በእኛ በኩል በማንኛውም ጊዜ አስፈላጊ ሥልጠናዎችንም ሆነ ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁ መሆናችንን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

አብርሃም ንጉሤ
ም/ዋና ዳይሬክተር
የሞደርናይዜሽንና ኮርፖሬት
ሥራዎች ዘርፍ

አባሪ፡

- 20 ገጽ

ግልባጭ

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለሀገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- ለመረጃ ቴክኖሎጂ ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት
- ለኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት
- ለደንበኞች አገልግሎት ዳይሬክቶሬት

ኢ.ገ.ጉ.ባ